<u>ደንብ ቁጥር 159/2016</u>

<u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ እንደገና ለመወሰን የወጣ ደንብ</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ላይ የሚደረግ የቁጥጥር ሁኔታን ለማሻሻል እና የልማት ድርጅቶቹ የአሠራር ውጤታማነታቸውንና የፋይናንስ አቋማቸውን ለማጠናከር የሚያስችላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የልማት ድርጅቶቹ ከግል ድርጅቶች ጋር በግልጽ ውድድር መሥራት የሚችሉበትን አቅም ለማጠናከርና ምርማነታቸውንና ትርፋማነታቸውን ለመጨመር ለንግድ ቅልጥፍና ያላቸውን አመለካከት የሚቀይር አመቺ የሆነ የቁጥጥር ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የልማት ድርጅቶቹ ተጠያቂነታቸውን በማረጋገጥና ግልጽነትን በማዳበር ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበትን ሥርዓት በመዘርጋት የኮርፖሬት አስተዳደራቸውን ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር ማጣጣሙ ጠቀሜታው የላቀ በመሆኑ፤

የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አፈጻጸማቸውን ማሻሻል እና የፊስካል ስጋትንና በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ላይ የሚያሳድሩትን ጫና መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ረ) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 159/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
   2. **"ከንቲባ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤
   3. **"ካቢኔ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ነው፤
   4. **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን ነው፤
   5. **"የልማት ድርጅት"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ ሙሉ ወይም በከፊል ባለቤትነት የማምረት፣ የማከፋፈል፣ የመገንባት፣ አገልግሎት የመስጠት፣ ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባሮችንና ከእነዚሁ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በንግድ መልክ ለማካሄድ በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ደንብ መሠረት የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነው፤
   6. **"ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን"** ማለት በልማት ድርጅቶች ውስጥ የአስተዳደሩን የባለቤትነት መብቶች በበላይነት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው የከተማ አስተዳደሩ ተቋም ነው፤
   7. **"ጠቅላላ ሀብት"** ማለት ካለፉት ኩነቶችና ከእነዚሁ የሚገኙ በልማት ድርጅቱ ይመጣሉ ተብለው የሚጠበቁ የወደፊት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ወይም እምቅ አገልግሎት ምክንያት በልማት ድርጅቱ ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት ነው፤
   8. **"የተጣራ ሀብት"** ማለት ዕዳዎችን ሁሉ በመቀነስ የሚገኘው በልማት ድርጅቱ ሀብት ውስጥ የሚገኝ ቀሪ የሆነ ጥቅም ነው፤
   9. **"ካፒታል"** ማለት የልማት ድርጅቱ በሚቋቋምበት ወቅት የሚመደብ የተጣራው ሀብት እሴት ነው፤
   10. **"የተጣራ ትርፍ"** ማለት የሥራ ማስኬጃ እና ከአጠቃላይ ገቢው ታክስን ወይም ግብርን፣ ወለድና የእርጅና ተቀናሽን ጨምሮ ሌሎች ክፍያዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚገኝ የልማት ድርጅቱ ትርፍ ነው፤

11."**የመንግስት የትርፍ ድርሻ**" ማለት ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ገቢ የሚሆነው ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረው ሂሳብ ነው፤

12.“**ኦዲተር**” ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 32 መሰረት የልማት ድርጅቱን ሂሣብ እንዲመረምር የተፈቀደለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13.”**ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ**” ማለት ኪሣራንና ዕዳን፣ የንብረት መጠበቂያን ወይም መጠገኛን እና ኢንቨስትመንትን የመሳሰሉ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ወደፊት ለሚያጋጥሙ ያልታሰቡ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚውል ከተጣራ ትርፍ በመቀነስ በልማት ድርጅቱ በመጠባበቂያነት የሚያዝ ገንዘብ ነው፤

14.”**ቦርድ**” ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 መሠረት የተቋቋመ የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው፤

15.”**የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ**” ማለት በዚህ ደንብ እና በልማት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንብ ወይም ከንቲባው በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የልማት ድርጅት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ የተጣለበት ግዴታ ነው፤

16.”**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

17.በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

3. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **<u>ዓላማዎች</u>**

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የልማት ድርጅቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ውጤታማነትን፣ አትራፊነትንና ተወዳዳሪነትን ግባቸው አድርገው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ፤
2. በልማት ድርጅቶች ላይ አስተዳደሩ የሚያፈሰው ኢንቨስትመንት ወይም ሀብት በልማት ድርጅቶቹ ደረጃ በቂ ትርፍ እንዲያገኝ ማድረግ፤
3. የልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የሥራ አመራራቸውንና ለሕዝብ አገልግሎቶች የመስጠት ግዴታቸውን በውጤታማነትና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፤

4. የልማት ድርጅቶች በካንቲባው አማካኝነት በሚሰጥ የመንግስት አቅጣጫ የሕዝብ አገልግሎት ግዴታቸውን ሲወጡ ግልጽነት የተላበሰ የወጪ እና የፋይናንስ ማዕቀፍ እና የክትትል ሥርዓት በሥራ ላይ ያዋሉ መሆናቸውን እና በንግድ ላይ ያተኮረው ተልዕኮዋቸው ለድርድር ያልቀረቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
5. የልማት ድርጅቶች አስተዳደርና አመራር ኃላፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት በተላበሰ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና የኮርፖሬት ፋይናንስ እየተገበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
6. ከልማት ድርጅቶቹ ፋይናንስ፣ ሂሣብ አያያዝና አሠራር ጋር በተያያዘ ውጤታማ ቁጥጥር እና የሥራ እንቅስቃሴዎችና ክንዋኔ ግምገማ መኖሩን ማረጋገጥ፤
7. የቴክኖሎጂ ሽግግርን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመፈፀም የማምረት አቅም በመጨመር የከተማውን ኢኮኖሚ እድገት ማፋጠን፤
8. የፊስካል ዘለቄታማነትን ማሳደግ እና የፊስካል ስጋቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ መመራታቸውን ማረጋገጥ፤
9. የልማት ድርጅቶች ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ለማኅበራዊ ልማት እና ለሥራ ፈጠራ ከተማ አቀፍ ዓላማዎች አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ ማስቻል፤ እና
10. የልማት ድርጅቶቹ በቅጥር ፖሊሲዎቻቸውና አሠራራቸው የፆታ እኩልነትን የሚያራምዱ በብቃት ላይ የተመሠረተ ሙያና አቅም ያላቸውን ሠራተኞች የሚቀጥሩ ጥሩ አሠሪዎች እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የልማት ድርጅቶችን ስለ መቋቋም፣ ሕጋዊ ሰውነት እና ችሎታ</u>

5. <u>የልማት ድርጅት ምሥረታ</u>
   1. የልማት ድርጅት በካቢኔ ሊቋቋም ይችላል፤
   2. ካቢኔው የሚያቋቁመውን የልማት ድርጅት በበላይነት የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይመድባል፤
   3. የልማት ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት የሚከተሉት መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡-
      ሀ) አስተዳደሩ ድርጅቱን ለማቋቋም አሳማኝ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች መኖራቸውን፣

ለ) ለማቋቋሚያ ካፒታል በዓይነት የተዋጣ ክፍያ ካለ ዝርዝር የንብረቱን መግለጫ፣ የእያንዳንዱን ንብረት ዋጋ ግምትና የአገማመቱን ዘዴዎች በባለሙያ በትክክል መገመቱን፤ እና

ሐ) ለመነሻ ካፒታል ተብሎ የተከፈለ ማናቸውም ጥሬ ገንዘብ የልማት ድርጅቱ እንደተቋቋመ በስሙ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ መቀመጡን፤

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ለ) ቢኖርም፣ በዓይነት የተፈጸመው ክፍያ ኦዲት የተደረገ ሂሣብ ካለው በሂሣብ መዝገብ የተመለከተው የዓይነት ክፍያ ሊወሰድ ይችላል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ለ) የተጠቀሱት ባለሙያዎች በዓይነት የተዋጣውን ንብረቶች ዝርዝር መግለጫ፣ ለእያንዳንዱ ንብረት የተሰጠውን ዋጋ እና የአገማመቱን ዘዴዎች ያካተተ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፤

6. የልማት ድርጅትን ለማቋቋም አስተዳደሩ ያወጣው ኦዲት የተደረጉ ማናቸውም ወጪዎች የልማት ድርጅቱ መነሻ ካፒታል አካል ይሆናሉ፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ሐ) ተቀማጭ የሆነው ገንዘብ የልማት ድርጅቱ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እስከሚያገኝ ወይም ማቋቋሚያው ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ እስከሚወጣ ድረስ በዝግ አካውንት የሚቀመጥ ይሆናል።

6. <u>ማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ሕግ</u>

1. ባለቤትነቱ ሙሉ በሙሉ ወይም አብላጫ ድርሻው በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት የሚቋቋመው በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ደንብ ነው፤

2. የልማት ድርጅት መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም ማቋቋሚያ ደንብ፡-

ሀ) የልማት ድርጅቱ ስም፣

ለ) የልማት ድርጅቱ በዚህ ደንብ የሚገዛ መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፣

ሐ) የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት የንግዱ ዓላማ እና የሚሳተፍበት አትራፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣

መ) የልማት ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ፣

ሠ) የተፈቀደው ካፒታል፣

ረ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተከፈለው ካፒታል መጠን፤

ሰ) የልማት ድርጅቱ ከጠቅላላ ሀብቱ በላይ ሊጠየቅ እንደማይችል የሚገልጽ ድንጋጌ፤

ሸ) የልማት ድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት አድራሻ፤

ቀ) የልማት ድርጅቱ ቅርንጫፍ መክፈት እንደሚችል የሚገልጽ ድንጋጌ፤

በ) የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ስም፣ እና

ተ) የልማት ድርጅቱ የቆይታ ጊዜ መያዝ ይኖርበታል፡፡

7. <u>ሕጋዊ ሰውነት እና ተጠያቂነት</u>

1. የልማት ድርጅቱ መብቶችና ግዴታዎች የሚያጎናጽፉት ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል፤
2. የልማት ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

8. <u>የልማት ድርጅቱ አድራሻና ድኅረ-ገጽ</u>

1. የልማት ድርጅቱ አድራሻ ዋናው መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ ነው፤
2. ሁሉም በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚከተሉትን መረጃዎችን የያዘ ድኅረ ገጽ ሊኖራቸው ይገባል፡-

ሀ) ወቅታዊ ኦዲት የተደረገ የኦዲት ሪፖርትና የኦዲቱ ግኝት፣

ለ) ዓመታዊ ሪፖርት፣

ሐ) የልማት ድርጅቱ የቦርድና የሥራ አስፈጻሚዎች መረጃዎች፤

መ) ቦርዱ ከንግድና ስትራተጂክ አንፃር ሚስጥራዊ ናቸው ካላቸው ውጭ ያሉ የቦርድ ቃለ ጉባዔዎችና ውሳኔዎች፤ እና

ሠ) ለሕዝብ ጠቃሚ የሆነ የልማት ድርጅትን የሚያመለክት ሌላ ማንኛውም መረጃ፡፡

9. <u>ችሎታ</u>

1. የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ እና በመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በማቋቋሚያ ደንቡ ከተመለከቱት የሥራ ዝርዝሮች ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችለው ችሎታ ይኖረዋል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቱ፡-

ሀ) በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ እና በግልግል ዳኝነት ፊት ድርጅቱን የመወከል፤

ለ) የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትን በግዢ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የማግኘት፣ ባለይዞታ የመሆን፣ ባለቤት የመሆን፣ በማያገሮ የመስጠት፤

ሐ) ውል የመዋዋል፣ ገንዘብ የመበደር፤

መ) የንግድና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን የማውጣትና የመቀበል፤

ሠ) የባንክ ሂሣብ የመክፈትና የማንቀሳቀስ፤ እና

ረ) የዚህ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ለ) ፣ (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ኢንቨስት የማድረግ፤ችሎታ ይኖረዋል፤

3. ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር የልማት ድርጅቶቹ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፡-

ሀ) ከአጠቃላይ ሀብቱ ከ50 % (ሃምሣ በመቶ) በላይ የሆነ ዕዳ ውስጥ መግባት፣

ለ) በጋራ ኢንቨስትመንት መሳተፍ፤ እና

ሐ)ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት የሚጠየቅ በሕግ የተመለከተ ማናቸውንም ነገር፡፡

ክፍል ሶስት

የልማት ድርጅቶቹ ተወዳዳሪነት

10. **ተወዳዳሪነት ያለበት የንግድ ከባባዊ ሁኔታ**

1. የልማት ድርጅቱ አስተዳደሩ በባለቤትነት የያዘው በመሆኑ ከሌሎች የንግድ ድርጅቶች በተለየ ተጠቃሚም ሆነ ተጎጂ መሆን የለበትም፤

2. የልማት ድርጅቱ የዘመናዊ ኮርፖሬት አስተዳደር መዋቅሮች ደንብና ፖሊሲዎች፣ የፋይናንስ የተጠያቂነት እና የሥራ አፈፃፀም አስተዳደር ሥርዓቶች እና እንቅስቃሴው የገበያ ማዛበትን አለማስከተሉን ለማረጋገጥ በዘርፉ ተፈጻሚ የሚሆን የአገላለጽ መስፈርቶችን በመተግበር ተወዳዳሪ በሆነ የንግድ ከባባዊ ሁኔታ ውስጥ መንቀሳቀስ አለበት፤

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጹት የማስፈጸሚያ ሥርዓት ባሟላ ሁኔታ የልማት ድርጅቱ የሕዝብ አገልግሎት እንዲያቀርብ ግዴታ ሊጣልበት ይችላል፡፡

11. የህዝብ አገልግሎት ግዴታዎች

1. በከንቲባው አማካኝነት በሚቀርብ ጥያቄ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የልማት ድርጅትን ከመመሥረቻ ጽሁፉ ወይም ከማቋቋሚያ ደንቡ ጋር የሚጣጣም የሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም እንዲያቆም በጽሑፍ ግዴታ ሊጥልበት ይችላል፤
2. የሚቀርበው የሕዝብ አገልገሎት ግዴታ ጥያቄ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

   ሀ) የሚቀርበውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዓይነት፣

   ለ) የሕዝብ አገልግሎት ግዴታውን ለመወጣት በልማት ድርጅቱ ላይ የሚያስከትለው ዓመታዊ አጠቃላይ ወጪ በግምት፣

   ሐ) የሕዝብ አገልግሎት ግዴታውን በመወጣት በልማት ድርጅቱ የሚገኘው ዓመታዊ ትርፍ ወይም የሚደርስበት ኪሣራ በግምት፤

   መ) የገንዘቡን ምንጭ እና የህዝብ አገልግሎት ግዴታን ለመወጣት ከከንቲባው ወይም ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ፈቃድ፤

   ሠ) የልማት ድርጅቱ የህዝብ አገልግሎት ግዴታውን በሚወጣበት ጊዜ እንዴት ቁጥጥር እንደሚደረግበትና አፈጻጸሙ እንደሚለካ፤ እና

   ረ) የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ አፈጻጸም ለሕዝብ ስለሚገለጽበት ዘዴዎች፡፡

ክፍል አራት

የልማት ድርጅቶች አስተዳደራዊ መዋቅርና ሥራ አመራር

12. ድርጅታዊ መዋቅር

እያንዳንዱ የልማት ድርጅት፡-

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ፤
2. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤
3. ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

13. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባራት

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላትን ይመለምላል፣ ለከንቲባ ያቀርባል፤

2. በቦርድ አባላት መካከል የዖታ መመጣጠንን ለማምጣት እርምጃዎችን ይወስዳል፤
3. የቦርድ አባላትን ለመሾምና ለማሰናበት ተፈጻሚ የሚሆኑ ዘመናዊ የኮርፖሬት እና የፋይናንስ አስተዳደር ልምዶች ጋር የሚጣጣሙ መመሪያዎች ያወጣል፣ በተግባር ላይ ያውላል፤
4. በቅድሚያ ስምምነት በተደረሰባቸው የሥራ አፈጻጸም ምዘና መስፈርቶች መሠረት የቦርዱንና የግለሰብ ቦርድ አባልን የሥራ አፈጻጸም በየዓመቱ ይመዝናል፣ እንደአግባቡ ማበረታቻ ይሰጣል፤
5. አግባብ ባለው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሕጎች መሠረት ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር እና የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ አሰራሮችን አዘጋጅቶ ያወጣል፤ የልማት ድርጅቶቹ እየተተገበሩት መሆኑን ይከታተላል፤
6. ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ወይም በሥራ ላይ እያሉ ስለ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር ልምዶች ለሁሉም ቦርድ አባላት ሥልጠና ይሰጣል፤
7. የልማት ድርጅቶችን የሥራ አፈጻጸም ለማሻሻል፣ በሥራቸውም ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትንና ተወዳዳሪነትን እንዲኖር ለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቶችን አዘጋጅቶ ያወጣል፤
8. በልማት ድርጅቶች የሚቀርቡ የካፒታል ማሳደግና መቀነስ ጥያቄዎችን ይገመግማል፣ በዚህ ደንብ አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤
9. የልማት ድርጅቶች የመንግሥትን የባለቤትነት ፖሊሲ በመንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መሠረት ከንቲባውን በማማከር ተግባራዊ ያደርጋል፤
10. የፊስካል ስጋቶችን ለመቀነስ በከንቲባው የወጡ እርምጃዎችን መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
11. የልማት ድርጅቶቹ ዓመታዊና የረጅም ጊዜ የንግድ ዕቅዶች ማዘጋጀታቸውን እና ፋይናንስ ነክና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የሥራ አፈጻጸም እርምጃዎችንና የንግድ ዕቅዶቹን ለመተግበር እና ስትራቴጂውንና የንግድ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ቁልፍ የሥራ አፈጻጸም መለኪያዎችንና ግቦችን ጨምሮ የንግድ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ በየዓመቱ ከቦርድ ጋር የሥራ አፈጻጸም ስምምነት ይፈራረማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሲሆን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፤

12.የልማት ድርጅቶቹ ትክክለኛ ክህሎት፣ ሙያ፣ ልምድና ብቃት ባላቸው ግለሰቦች መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፤

13.የልማት ድርጅቶቹ ለምርምርና ልማት እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ሽግግር በጀት የሚመደቡበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ የምርምሩን ግኝቶችንም ያሰራጫል፤

14.የልማት ድርጅቶቹ በዚህ አዋጅ መሠረት ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ እንዲያቋቁሙ ያደርጋል፤

15.አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለተቋቋሙ በመንግሥት ባለቤትነት ለተያዙ የልማት ድርጅቶች በከተማ አስተዳደሩ ገንዘብ መመደቡን እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለልማት ድርጅቶቹ የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ መከፈሉን ያረጋግጣል፤

16.የልማት ድርጅቶቹ ለአስተዳደሩ የሚከፍሉትን የመንግሥት የትርፍ ድርሻ መጠንን የውሳኔ ሃሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰን ተግባራዊ ያደርጋል፤

17.የፋይናንስና የሥራ አፈጻጸም መለኪያዎችን በመጠቀም የልማት ድርጅቶቹን ሥራ አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ የልማት ድርጅቶቹን የሥራ አፈጻጸም ዓመታዊ የተጠቃለለ ሪፖርት በድኀረ ገጹ ያወጣል፤

18.የልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርት ያፀድቃል፣ በኢ.ዲት ምርመራ ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

19.በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አግባብ ባለው የፌደራል መንግስት ሕግ መሰረት የልማት ድርጅቶች ሂሣብ ስለሚሰረዙበት ሁኔታ ለከንቲባው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

20.በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሥር ያሉ የልማት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደሩ የሚኖረውን የባለቤትነት መብት በተመለከተ የአስተዳደሩ ተወካይ በመሆን የአስተዳደሩን አክስዮን በባለቤትነት ይይዛል፤

21.የልማት ድርጅቱ በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፋይናንስ አቋሙን ለማስተካከል ቦርዱ በቂ እርምጃ አልወሰደም የሚል አስተያየት ካለው፤ የልማት ድርጅቱ የቦርድ አባላት በአዲስ የቦርድ አባላት እንዲተኩ ለከንተባው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

22. ሊያጋጥሙ የሚችሉ የፊስካል ስጋቶችን ለመከታተልና ለመገምገም አስፈላጊ የሆኑ የቦርድ ኮሚቴዎች ሪፖርቶችን ጨምሮ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን ሁሉ ከልማት ድርጅቶቹ ይሰበስባል፤

23. ከሰበሰበው መረጃና ሪፖርቶች በመነሳት የልማት ድርጅቱን የዕዳ ሸክም እና ዕዳው በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የግምገማ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ የፊስካል ስጋቶች መቀነሻ እርምጃዎችን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፤

24. የድርጅቶቹን የፊስካል ስጋቶችና በመንግሥት ሂሣቦች ላይ ስለሚኖራቸውን እምቅ ተፅዕኖ ዓመታዊ ሪፖርት፣ የልማት ድርጅቱ የተሰማራበት ዘርፍን፣ የፋይንስ ሁኔታ የሩብ ዓመት ሪፖርቶች እና ሁኔታው በሚያስገድድበት ጊዜ ለሚመለከተው የልማት ድርጅት የስጋቶች መቀነሻ እርምጃዎች ሪፖርት ያዘጋጃል፤

25. የልማት ድርጅቱ በከፍተኛ ደረጃ ለፋይናንስ እጥረት ተጋላጭ ሆኖ ወይም እጥረት አጋጥሞት ከተገኘ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ፡-

    ሀ) በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የድርጅቱን የፋይናንስ አቋም እንዲያሻሽሉ ገምግሞ ለቦርዱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

    ለ) የልማት ድርጅቱ አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፋይናንስ አቋሙን ለማስተካከል ምንም ዓይነት ወይም በቂ የሆኑ እርምጃዎች አልተወሰዱም የሚል አስተያየት ካለው የልማት ድርጅቱ የቦርድ አባላት እንዲተኩ እና አዲስ የቦርድ አባላት እንዲሾሙ ለከንቲባው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

14. <u>በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር</u>

1. በከንቲባው አመራር እና አቅጣጫ መሠረት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የአዋጭነት ጥናት በማጥናት ወይም በማስጠናት፣ ለካቢኔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቶቹ የሚሸጡት ወይም ወደ ግል የሚዛወሩት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

15. **ስለቦርድ መቋቋም**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 የተሰጡትን ኃላፊነቶችን ለመወጣት እና የድርጅትን ጥቅም ለማስጠበቅ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይኖረዋል፤
2. ማንኛውም ቦርድ በማናቸውም ጊዜ ሥራውን በልማት ድርጅቱ ስምና ለድርጅቱ የላቀ ጥቅሞች በተገቢው ጥንቃቄ ማከናወን አለበት፤
3. ቦርዱ ከሚያጋጥሙና ሊያጋጥሙ ከሚችሉ የጥቅም ግጭት ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፤
4. ቦርዱ ሰብሳቢውን እና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ ከአምስት ያላነሱ ከዘጠኝ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል፤
5. አንድ የቦርድ አባል ከሠራተኞች መካከል በሠራተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል፡ የሠራተኞች ማኅበር መሪ የቦርድ አባል ሊሆን አይችልም፤
6. የቦርድ አባላት በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የወጡትን መመሪያዎችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፤
7. የቦርድ አባላት የልማት ድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዝ የትምህርት ደረጃ፣ ክህሎትና ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው፤
8. ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ከአንድ ሦስተኛ ያላነሱት አግባብነት ያለው ሙያ እና ከአምስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያላቸው ገለልተኛ የቦርድ አባላት መሆን አለባቸው፤
9. የቦርድ አባላት መልካም ስም ያላቸው እና ለሹመት ከመታጨታቸው በፊት ላሉት ሦስት ዓመታት በቦርድ አባልነት ለሚሾሙበት የልማት ድርጅት ሠራተኞች ያልነበሩ፣ ከልማት ድርጅቱ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ የገንዘብ፣ ቤተሰባዊ፣ የንብረት፣ የሙያ ትርጉም ያለው ግንኙነት ጨምሮ ማናቸውም የግል ጥቅም ያልነበራቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤
10. ማንኛውም የቦርድ አባል ከሦስት ለማይበልጡ ተወዳዳሪ ላልሆኑ ለሌሎች የልማት ድርጅቶች በተመሳሳይ ጊዜ በቦርድ አባልነት በመሾም ሊያገለግል ይችላል፤
11. የቦርድ አባል የሚሾመው ለሦስት ዓመት የሥራ ዘመን ሆኖ ለሁለተኛ ጊዜ እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡ የቦርዱ የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እንዲያበቃ አይደረግም፤

12. ማንኛውም የቦርድ አባል ከሥራው በፈቃደኝነት ሲለቅ ቦርዱ ጉዳዩን አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በአምስት ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፣ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት በለቀቀው የቦርድ አባል ምትክ ለቀሪው የሥራ ዘመን የሚያገለግል ሌላ የቦርድ አባል እንዲሾም ለከንቲባው ያቀርባል፣
13. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በቂና አሳማኝ ምክንያቶች ሲኖሩ ለአባልነት የማይመጥንን አንድ የቦርድ አባል በማንኛውም ጊዜ ከአባልነት እንዲነሳ ለከንቲባ ያቀርባል፣ ሲወሰን ከአባልነት ለሚነሳው ሰው በጽሁፍ ያሳውቃል፣ ይህ ድንጋጌ በሠራተኛ በተመረጠ የቦርድ አባል ላይ ተፈጻሚ የሚሆን እንደሆነ ተተኪ የቦርድ አባል እንዲመርጥ የቦርድ አባሉን መሰናበት ጠቅላላ ጉባዔው እንዲያውቀው ይደረጋል፣
14. የሁሉም ቦርድ አባላት ሹመት፣ ስንብትና መልቀቂያ ሁኔታው በተከሰተ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ሹመቱ፣ ስንብቱ ወይም መልቀቂያው እንደአግባቡ በልማት ድርጅቱ ወይም አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ድኅረ ገጽ መውጣት ይኖርበታል፡፡

16. <u>የቦርድ አባላት ምልመላና ሹመት</u>

ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ፡-

1. የቦርድ አባላት ምልመላ፣ ስብጥር፣ ምደባ እና ስንብት መስፈርት ያወጣል፣
2. የልማት ድርጅቱን የቦርድ አባላት በመመልመል እንዲሰየሙ ለከንቲባ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰን ያስፈጽማል፡፡

17. <u>ስለቦርድ አባላት ማበረታቻና ስንብት</u>

ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ፡-

1. የልማት ድርጅት የቦርድ አባላት ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ፣ ከድርጅቱ ፋይናንስ ጤንነት አጠባበቅ እና ከድርጅቱ ዕቅድ አፈጻጸም አንጻር ውጤታማ አፈጻጸም ላሳዩ የማትጊያና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ይተገብራል፣
2. የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያልተወጡ ወይም መፈጸም ያልቻሉ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከልማት ድርጅት የቦርድ አባልነት ስለሚሰናበቱ ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት አዘጋጅቶ ለከንቲባ ያቀርባል፣ ሲወሰን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

18. <u>የቦርድ ስብሰባ እና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>

1. የልማት ድርጅቱ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ያለውን ጊዜ ጨምሮ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የቦርዱ ሰብሳቢ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ወይም ቢያንስ ሁለት የቦርድ አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
3. የቦርዱ አጀንዳ ከስብሰባው ቀን ቢያንስ ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ሁሉም አባላት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቦርድ ስብሰባ በሰብሳቢው የተጠራ እንደሆነ የቦርዱ የስብሰባ አጀንዳ ከስብሰባው ጥሪ ጋር እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፤
5. ሰብሳቢውን ጨምሮ በማገልገል ላይ ያሉ ከግማሽ በላይ የቦርድ አባላት በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው ይሆናል፤
6. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የቦርዱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
7. ቦርዱ ለሥራው ድጋፍ የሚያደርግለት የቦርድ ፀሐፊ ይቀጥራል ወይም እንዲመደብ ያደርጋል፤
8. የልማት ድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በቦርድ ስብሰባ ይሳተፋል፤ ሆኖም ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፤
9. ቦርዱ ለእያንዳንዱ ስብሰባ በስብሰባው የተገኙ አባላት የፈረሙበት ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፤
10. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

19. <u>የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ቦርዱ፡-

ሀ) በዚህ ድንብ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ እንዲፀድቁ ከሚቀርቡት በስተቀር የልማት ድርጅቶች የፋይናንስ ዕቅድ፣ ቁልፍ የሥራ አፈጻጸም መለኪያዎች እና ስትራተጂክ አቅጣጫ ያካተተ የኮርፖሬት ፖሊሲንና የንግድ ዕቅድን ያፀድቃል፤

ለ) ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር ብቃትንና በዘርፉ ያለውን ልምድን ጨምሮ ችሎታን እና በግልጽ በተቀመጠ የምልመላ መስፈርቶችን መሠረት በውድድር ላይ በተመሠረተ የምልመላ ሂደት ለልማት ድርጅቱ ዋና እና ምክትል ሥራ አስፈጻሚነት የሚቀጠሩ እና የሚሾሙትን ይለያል፣ ለውሳኔ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፤

ሐ) ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ጋር በመካከር ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ የሥራ አመራር አባላትና ሠራተኞች የልማት ድርጅት የሥራ አፈጻጸምንና ትርፋማነትን መሠረት በማድረግ ማበረታቻና የደሞዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

መ) ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ የልማት ድርጅት ኃላፊዎችን ምደባና ስንብት ያፀድቃል፣

ሠ) ዋነኛ የድርጊት ዕቅዶችን፣ የስጋት አስተዳደር እና ትግበራ ፖሊሲንና ሥርዓቶችን ይገመግማል፣ አመራር ይሰጣል፣

ረ) ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ባወጣው ማዕቀፍ መሠረት ዓመታዊ በጀትን ያፀድቃል፣ የሥራ አፈጻጸም ዓላማዎችን ይደነግጋል፣

ሰ) የልማት ድርጅቱን የውስጥ ደንቦች እንዲሁም የሥራ ፕሮግራም ያፀድቃል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤

ሸ) ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር ከፀደቀው የንግድ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ የልማት ድርጅቱን ብድር እና በመያዣነት የሚሰጥ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ያፀድቃል፤

ቀ) የልማት ድርጅቱ ንብረት በአግባቡ መጠበቁን ያረጋግጣል፣ የልማት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድር የቋሚ ንብረት ሽያጭን ያፀድቃል፤

በ) የልማት ድርጅት የሂሣብ መዝገብ የድርጅቱን የሂሣብ አያያዝና ተፈጻሚነት ያላቸው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በተከተለ መንገድ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፤

ተ) የሂሣብ መዝገብ ለልማት ድርጅቱ፣ ለኦዲተሮች እና ለዋናው ኦዲተር ዋና ኦዲተሩ በሚወስነው የመዝገብ አቀራረብ መሠረት የድርጅቱን ወቅታዊ የፋይናንስና ሌሎች ሪፖርቶች ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፤

ቸ) የልማት ድርጅትን የሩብ ዓመት፣ የመንፈቅና ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫዎችን ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ያፀድቃል፤

ኀ) የልማት ድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና ሌሎች ማናቸውንም ሪፖርቶች በሚወስነው የሪፖርት አቀራረብ መሠረት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፤

ነ) የልማት ድርጅት ዕዳን የመቋቋም አቅምን ለኢንዱስትሪው በተቀመጡ ደረጃዎች መሠረት ለማስተዳደር በዘርፉ ተፈጻሚ የሚሆን ዘላቂ የዕዳና የሀብት ቀመር እንዲወሰን ያደርጋል፤

ኘ) የልማት ድርጅቱን ካፒታል መጨመርንና መቀነስን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሃሣብ ያቀርባል፤

አ) የልማት ድርጅቱ ቦርድና ሠራተኞች የሚተዳደሩበት የሥነ-ምግባር መመሪያ ያፀድቃል፤ ይዘቱንና አፈጻጸሙን ቢያንስ በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ ይገመግማል፤

ከ) የልማት ድርጅቱን የመንግሥት አገልግሎት ግዴታዎች አፈጻጸምና ስኬት በመደበኛነት ለሕዝብ መረጃዎች መተላለፋቸውን ያረጋግጣል፤

ኸ) የልማት ድርጅቱ ንብረት ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፤ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

ወ) በልማት ድርጅቱ እና የቦርድ አባላት ወይም የሥራ ኃላፊዎችን መካከል የጥቅም ግጭት ሲኖር ተገቢ ውሳኔ ይሰጣል፤

የ) ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም ሰነዶች ያቀርባል፡፡

2. ቦርዱ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የልማት ድርጅቱንና ካለ የተቀጥላ ድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴን፣ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን እና የፋይናንስ ትንበያዎችን የያዘ በበጀት ዓመቱ እና በቀጣዮቹ የበጀት ዓመታት ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የንግድ ዕቅድ ያፀድቃል፤

3. የንግድ ዕቅዱና በዕቅዱ የተካተቱት መረጃዎች በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ከወጡት መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፤

4. ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከሦስት ወር በፊት በበጀት ዓመቱ ተፈጻሚ የሚሆነውን የመጨረሻውን የንግድ ዕቅድ ረቂቅ ያቀርባል፤
5. ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በረቂቁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የንግድ እቅዱን ማጽደቅ አይችልም፤
6. የንግድ ዕቅዱን ባፀደቀ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ኮፒውን ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፤
7. የልማት ድርጅቱ የንግድ ዕቅዱን በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል ሆኖም ቦርዱ፡-
   ሀ) የተሻሻለውን የመጨረሻ ረቂቅ ከማጽደቁ ቢያንስ ከሁለት ወር በፊት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፤
   ለ) ከተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በረቂቁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ማሻሻያውን ማጽደቅ አይችልም፤
   ሐ) ማሻሻያውን ባፀደቀ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ኮፒውን ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

20. <u>የቦርድ አባላት ተግባራትና ኃላፊነቶች</u>

1. የልማት ድርጅቱ የቦርድ አባላት፡-
   ሀ) የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ማድረሱን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃዎች ይወስዳል፣
   ለ) የንግድ ሕጉን እና ተፈጻሚነት ያለውን ዘመናዊ ኮርፖሬት አስተዳደርን መሠረት በማድረግ ኃላፊነቶቹን በቅን ልቦናና ለልማት ድርጅቱ የላቀ ጥቅም በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን አለበት፤
   ሐ) የልማት ድርጅቱ የሚገባውን የዕዳ መክፈያው በሚደርስበት ወይም መክፈል በሚኖርበት ጊዜ መክፈል የማይችል የሆነ እንደሆነ ድርጅቱ ዕዳ ውስጥ እንዳያገባ ተገቢውን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል፤
   መ) በቦርድ አባልነቱ ምክንያት ያገኘውን መረጃዎች ለአግባብ ጥቅም ላይ ማዋል አይችልም፤
   ሠ) በልማት ድርጅቱ ቦርድ አባልነታቸው ተግባራቸውን ወይም ሥራቸውን በተገቢው መንገድ እንዳያከናውኑ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉባቸውን ማናቸውንም የጥቅም ግጭቶች ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

2. ማናቸውም የቦርድ አባል በዚህ ደንብ መሠረት ሥራውን ሳያከናውን የቀረ እንደሆነ ተግባሩን ባለመወጣቱ ምክንያት በልማት ድርጅቱ ላይ ለደረሰው ኪሣራ ወይም ጉዳት አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም ለኪሣራው ወይም ጉዳቱን ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሲተላለፍ ተቋውሞውን ያስመዘገበ የቦርድ አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

21. <u>ስለኮሚቴዎች</u>

1. ቦርዱ የተወሰነ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ተግባርና ኃላፊነቶቹ በግልጽ የተሰጡት የኦዲት፣ የስጋት አስተዳደር፣ የሥነ ምግባር እና ሌሎች ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል፤

2. የኦዲት እና የስጋት አስተዳደር ኮሚቴዎች ተገቢው የፋይናንስ ልምድ ያለው ቢያንስ አንድ አባልን የሚያካትት፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገጉትን መስፈርቶች በሚያሟላ የቦርድ አባል ሰብሳቢነት መመራት ይኖርባቸዋል፤

3. የልማት ድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ አመራር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኮሚቴ ስብሰባዎች ሊሳተፍ ይችላል፡፡

22.<u>የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣን፣ ተግባራትና ተጠያቂነት</u>

1. የልማት ድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪነቱ ለልማት ድርጅቱ ቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ) በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

   ለ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ግንኙነቶች ሁሉ እና የልማት ድርጅቱ በሚከስበትና በሚከሰስበት ጉዳይ የልማት ድርጅቱን ይወክላል ወይም ድርጅቱ በሚከስበት ወይም በሚከሰስበት ጉዳይ በእርሱ ስም የሚቀርብ ሕጋዊ ተወካይን ይሾማል፤

   ሐ) የልማት ድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፤ በቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ መዘርዝራቸውን ይወስናል፤

   መ) የልማት ድርጅቱን የውስጥ ደንቦችና የድርጅቱን ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ይመድባል፤ ያሰናብታል፤ ደሞዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፤

ሠ) በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዘውን የልማት ድርጅት አግባብነት ያለውን የሂሣብ መዝገብ ይይዛል፤ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የሂሣብ መግለጫዎች ያዘጋጃል፤

ረ) የልማት ድርጅቱን የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤ ሆኖም የባንክ ሂሳቡን ሲከፍት ወይም ሲዘጋ ለቦርድ ያሳውቃል፤

ሰ) በበጀቱ በተፈቀደው እና ከንግድ ዕቅዱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በአስተዳደሩ ባለቤትነት ለተያዘው የልማት ድርጅት የሥራ ማከናወኛ ካፒታል ከስድስት እስከ አሥራ ስምንት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከፈል የአጭር ጊዜ ብድር ስምምነት መዋዋል ይችላል፤

ሸ) በቦርድ ሲፀድቅለት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ገንዘብ መበደር ይችላል፤

ቀ) የአጭር ወይም የረዥም ጊዜ የብድር ውሎች ለመዋዋል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሰ) እና (ሸ) መሠረት ለሚበደረው ብድር የልማት ድርጅቱ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ መስጠት ይችላል፤

በ) የልማት ድርጅቱ የውስጥ ደንቦች እንዲሁም የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ተ) በልማት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ በማያደርስ ሁኔታ ቋሚ ንብረቶችን ከንግድ ዕቅዱ በተጣጣመ ሁኔታ ቦርዱን በማስፈቀድ ሊሸጥ ይችላል፤

ቸ) የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

ኀ) ሪፖርቶችን ለቦርድ ያቀርባል፤

ነ) የልማት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ በሆነ መጠን ሥልጣኑን ለድርጅቱ ሥራ ኃላፊዎች በውክልና ይሰጣል፤

ኘ) የልማት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ምክር የሚሰጥ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባዎችንም በሰብሳቢነት ይመራል፤

አ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

ከ) ዋና ሥራ አስፈጻሚው በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በልማት ድርጅቱ ላይ ላደረሰው ጉዳት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

23. ውክልና

የልማት ድርጅቱ በዋና ሥራ አስፈጻሚው እና በዚህ ሕግ መሠረት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች ተወካዮች አማካይነት ሥራውን ያከናውናል፤ መብቶቹን ይጎናጸፋል፣ ግዴታ ይገባል፡፡

ክፍል አምስት

የልማት ድርጅቱ ካፒታል

24. የልማት ድርጅቱን ካፒታል ስለማቋቋም

1. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የልማት ድርጅትን ለማቋቋም የሚስፈልገውን መነሻ ካፒታል እንዲመደብ ያደርጋል፤
2. ካፒታሉ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ሊከፈል ይችላል፤ በዓይነት የሚከፈል ከሆነ አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ለ) ወይም በሂሣብ መዝገቡ መሠረት ንብረቱ በባለሙያዎች በትክክል መገመቱን ያረጋግጣል፤
3. የንግድ ሕግ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የልማት ድርጅቱ በሚቋቋምበት ጊዜ የሚኖረው የተከፈለ የካፒታል መጠን ከተፈቀደው ካፒታል ከ25 በመቶ ያነሰ መሆን የለበትም፤
4. የተፈቀደውን ካፒታል 25 በመቶ በመክፈል የተቋቋመ የልማት ድርጅት የተፈቀደውን ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መክፈል ይኖርበታል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው መሠረት የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ ያልተከፈለ እንደሆነ የሦስተኛ ወገኖች መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተፈቀደውን ካፒታል ከተከፈለው ካፒታል መጠን እኩል በማድረግ ያስተካክለዋል፡፡

25. የተፈቀደ ካፒታል መጨመር ወይም መቀነስ

1. በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ካፒታል ለማሳደግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከልማት ድርጅቱ የተጣራ ትርፍ እንዲከፈል ያደርጋል፤

2. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የልማት ድርጅት ካፒታልን ለመጨመር የሚያስፈልገው ገንዘብ በአስተዳደሩ እንዲመደብ ወይም ከልማት ድርጅቱ የተጣራ ትርፍ እንዲከፈል ለከተማው አስተዳደር ካቢኔ የውሳኔ ሃሣብ ሊያቀርብ ይችላል፤
3. ሦስተኛ ወገኖች ያላቸው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል የሚቀነሰው፡-
   ሀ) ኦዲተሮች የተፈቀደው ካፒታል እንዲቀንስ ሃሣብ ሲያቀርቡ፤
   ለ) የልማት ድርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረብ ሃሣብን ተከትሎ የተፈቀደው ካፒታል እንዲቀንስ ከተወሰነ፤ እና
   ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (4) የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ ለሙሉ ካልተከፈለ ነው፡፡

ክፍል ስድስት

የልማት ድርጅት ስም እና የንግድ ስም

26.<u>የልማት ድርጅት ስም</u>

1. የልማት ድርጅቱ ስም የሚያከናውነውን ሥራ የሚገልጽ ስም ሆኖ ስሙም ሥራውን በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፤
2. የልማት ድርጅቱ ስም የመንግሥት ፖሊሲንና ሞራልን የሚቃረን እና የሦስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ መሆን የለበትም፤
3. የልማት ድርጅቱ ስም በማንኛውም የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ያልተመዘገበ መሆን አለበት፤
4. የልማት ድርጅቱ ስሙን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ በግልጽ እንዲታይ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

27.<u>የንግድ ምልክት</u>

1. የልማት ድርጅቱ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማናቸውንም ንግድ ምልክት ሊጠቀም ይችላል፤
2. የንግድ ምልክት ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት መመዝገብና ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ መውጣት ይኖርበታል፡፡

ክፍል ሰባት

የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ፈሰስ እና አጠቃቀም

28. የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ፈሰስ ስለማድረግ

1. የልማት ድርጅቶች ከዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ 5 በመቶ ካስቀሩ በኋላ በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (16) መሠረት በከንቲባው ሲወሰን የአስተዳደሩን የትርፍ ድርሻ ለአስተዳደሩ ገቢ ያደርጋሉ፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪው የትርፍ ድርሻ የልማት ድርጅቶች ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በጥናት ላይ የተመሰረተ ፕሮጀክት እያቀረቡ ሲፈቀድላቸው ጥቅም ላይ ሊያውሉት ይችላሉ፡፡

29. የትርፍ ድርሻ አጠቃቀም

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የሚፈቀድ የትርፍ ድርሻን ለመጠቀም የሚቀርብ ጥያቄ ከጥናት ሰነድ ጋር በልማት ድርጅቱ ቦርድ ተገምግሞና ፀድቆ በደብዳቤ መቅረብ አለበት፤
2. የሚፈቀደው የትርፍ ድርሻ በጥናት ላይ ተመስርቶ የልማት ድርጅቱን አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማሳለጥና ትርፋማ እንዲሆን በሚያስችል መንገድ የልማት ድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ መዋል አለበት፤
3. በዚህ ደንብ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት በአጠቃላይ ከትርፍ ድርሻ የሚፈቀደው ካፒታል፤ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች አዋጭነት፣ ፕሮጀክቶቹን ለመፈጸም የሚያስችል አመራር፣ አደረጃጀትና ክትትል ሥርዓት የተዘረጋበትና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር መኖሩ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ሲታመንበት ይፈቀዳል፤
4. የልማት ድርጅቶች በየበጀት አመቱ ሂሳባቸው በውጭ ኦዲተር ተረጋግጦ ከተጣራው ትርፋቸው ለከተማ አስተዳደሩ ወቅቱን ጠብቀው ፈሰስ እንዲያደርጉ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ያስፈጽማል፤
5. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት የማይፈፅም የልማት ድርጅት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

ክፍል ስምንት

የልማት ድርጅት ሂሣብ እና የኦዲት ምርመራ

30.የሂሣብ አያያዝ መርሆዎች

1. የልማት ድርጅትን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ለመወሰን በወጣው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ዓለም አቀፍ የሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎችን በመከተል የሂሣብ መዝገብ መያዝ እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ማዘጋጀት ይኖርበታል፤
2. የልማት ድርጅቱ እና እያንዳንዱ ተቀጥላ ድርጅት፡-
   ሀ) ግብይቶችን፣ የፋይናንስ አቋምንና የሥራ አፈጻጸምን በትክክል የሚመዘግብበትና የሚያስረዳ፤
   ለ) በዚህ ደንብ መሠረት የሂሣብ መግለጫዎች ለማዘጋጀትና የኦዲት ሥራ ለማከናወን የሚያስችል፤
   ሐ) በዚህ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የሚጠየቁትን የፋይናስ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የሚያስችል፤ በጽሑፍ የሰፈረ የፋይናንስ መረጃዎችን ይይዛል፡፡

31.የበጀት ዓመት

1. የልማት ድርጅት የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ሐምሌ 1 ጀምሮ ሰኔ 30 የሚያበቃው የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም የልማት ድርጅቱ አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ፈቃድ የተለየ የበጀት ዓመት መጠቀም ይችላል፡፡

32.ኦዲት ስለማድረግ

የልማት ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም በእርሱ በተሰየመ ኦዲተር ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን ባሟላ ሁኔታ ይመረመራል፡፡

33.ሪፖርት ስለማቅረብና መረጃን ስለመግለጽ

1. የልማት ድርጅቱ ሂሣቡን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መዝጋት ይኖርበታል፤ የዓመቱ የሂሣብ መዝጋት ሥራ የበጀት ዓመቱ ባበቃ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል፤

2. የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 እንደአግባቡ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ፣ በኦዲት ሥራና በመረጃ መግለጽ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

3. ዓመታዊ ሪፖርቱ፡-

   ሀ) በዚህ ደንብ የሚጠየቅ ከበጀት ዓመቱ ጋር የተያያዘ በኦዲተር የተመረመረ የፋይናንስ መግለጫዎችን ማካተት ይኖርበታል፤

   ለ) የፋይናንስ መግለጫዎቹን የሚመለከት የኦዲተር ሪፖርትን ማካተት ይኖርበታል፤

   ሐ) ከሪፖርቱ ጋር ተያያዥ በሆነው የበጀት ዓመት ውስጥ በልማት ድርጅቱ የተከናወነው ሥራ ለተጠቀሰው ዓመት በንግድ ዕቅዱ ከተቀመጠው ግቦች ወይም የሥራ መለኪያዎች አንፃር መገምገም ይኖርበታል፤

4. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የልማት ድርጅቱ ዓመታዊ ሪፖርት እንደደረሰው ለከንቲባ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

5. የልማት ድርጅቱ ሪፖርቱን ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ባቀረበ በአንድ ወር ውስጥ ሙሉ ዓመታዊ ሪፖርቱን በኦዲተር ከተመረመረው የፋይናንስ መግለጫዎች ጋር ለሕዝቡ ሊደርስ በሚችል የማስተላለፊያ ዘዴ እና በራሱ ድኅረ ገጽ ማውጣት ይኖርበታል፤

6. የልማት ድርጅቱ የበጀት ዓመቱን የሩብ እና የመንፈቅ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት የዓመቱ፣ የሩብ ወይም የመንፈቅ ዓመቱ ባበቃ በሁለት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የሩብ ዓመትና የመንፈቅ ሪፖርቶች፤

   ሀ) የልማት ድርጅቱ ወይም በስሩ ያሉ ተቀጥላ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ የንግድ ዕቅድ ከቦርዱ ጋር በስምምነት ያስቀመጡዋቸውን ግቦች ምን ያህሉን እንዳከናወኑ መግለጽ ይኖርበታል፤ እና

   ለ) ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የልማት ድርጅቱ እንዲያካትታቸው መመሪያ የተሰጠበትን ሌሎች ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡

34.<u>የልማት ድርጅቶች ሂሳብ መዝገብ ስለመሰረዝ፤</u>

1. ሂሳብ መዝገብ ለመሰረዝ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

    ሀ) በመሰብሰቢያና መክፈያ ጊዜ ውስጥ ሊሰበሰቡ ወይም ሊከፈሉ የማይችሉና አጠራጣሪ የሆኑ የተከፋይ ወይም የተሰብሳቢ ሂሳቦች፤

    ለ) ሊሰበሰቡ እንደማይችሉ የተረጋገጡ ሌሎች ሂሳቦች፤

2. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ሂሳቡን ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለከንቲባ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰን አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

35.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

በኦዲት ምርመራ ያለን የልማት ድርጅትን ገንዘብ የተቀበለ፣ የከፈለ ወይም ወጪ ያደረገ ወይም የድርጅቱ ንብረት በኃላፊነቱ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው ሲጠየቅ ሊመረመር የሚገባውን ሂሣብና አስፈላጊ መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

<u>ክፍል ዘጠኝ</u>

<u>የመጠባበቂያ ገንዘብና ታክስ</u>

36. <u>ስለመጠባበቂያ ገንዘብና አጠቃቀም</u>

1. እያንዳንዱ የልማት ድርጅት ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ማቋቋምና መያዝ ይኖርበታል፤

2. በሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች በተለየ መንገድ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ የልማት ድርጅት የካፒታሉን ሃያ በመቶ እስኪደርስ ድረስ በየዓመቱ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ አምስት በመቶ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ማስገባት አለበት፤

3. ሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘቡ ኪሣራን፣ ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

37. <u>ግብር ፣ታክስና ቀረጥ ስለመክፈል</u>

1. ግብር፣ ታክስንና ቀረጥን የሚመለከቱ አግባብ ያላቸው ሕጎች በልማት ድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች በአስተዳደሩ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በሌሎች

ሕጎች ከግብር፣ ከታክስና ከቀረጥ ነፃ የመሆንን እና ሌሎች መብቶችን የሚያስቀር አይሆንም፡፡

38.<u>የትርፍ ድርሻ ስለመክፈል</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የትርፍ ድርሻ የበጀት ዓመቱ ባበቃ በሰባት ወራት ውስጥ ለአስተዳደሩ መከፈል ይኖርበታል፡፡

<u>ክፍል አሥር</u>

<u>የልማት ድርጅት ውህደት፣ መከፈል</u>

39. <u>ስለውህደትና መከፈል</u>

1. የልማት ድርጅቱ ሌላ የልማት ድርጅትን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የልማት ድርጅቶችን በመጠቅለል ወይም አብሮ በመዋሃድ አዲስ ድርጅት ካቢኔው በደንብ ማቋቋም ይችላል፤
2. አንድ የልማት ድርጅትን ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ በመከፈል ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የልማት ድርጅቶች በካቢኔ ደንብ ሊቋቋም ይችላል፤
3. አንድ የልማት ድርጅት ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከመከፈሉ ወይም ከመቀላቀሉ በፊት ሂሳቡ ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡

40.<u>የተዋሃደ ወይም የተከፈለ የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ</u>

1. በውህደት ምክንያት ህልውናውን ያጣ የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለጠቀለለው የልማት ድርጅት ወይም በውህደት ለተፈጠረው አዲስ የልማት ድርጅት ሊተላለፍ ይችላል፤
2. የሚከፈል የልማት ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለተከፈሉት የልማት ድርጅቶች ስለሚመደቡበት ሁኔታ በአስተዳደሩ ካቢኔ ይወሰናል፤
3. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የመከፈሉን ውሳኔ እና መብትና ግዴታዎች ለተከፈሉት የልማት ድርጅቶች የሚከፋፈሉበትን መግለጫ የያዘ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፤
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በመከፈል የተፈጠረው እያንዳንዱ የልማት ድርጅት በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በተመደበላቸው የዕዳ መጠን ከመከፈሉ በፊት ለነበረው የልማት ድርጅት ገንዘብ ጠያቂዎች ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

<u>ክፍል አሥራ አንድ</u>

<u>የልማት ድርጅት መፍረስና ንብረት ማጣራት</u>

41.<u>የመፍረሻ ምክንያቶች</u>

የልማት ድርጅት በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

1. ካቢኔው የልማት ድርጅቱን ህልውና የሚነካ ውሳኔ ካስተላለፈ፤
2. በማቋቋሚያ ደንቡ ወይም በመመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሠረት የልማት ድርጅቱ የመቆያው ጊዜ ሲያበቃ፤
3. የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበትን ሥራዎች ሲያጠናቅቅ፤
4. በማቋቋሚያ ደንቡ ወይም በመመሥረቻ ጽሑፉ የተደነገጉት ዓላማዎች የማይሳኩ ወይም የማይፈጸሙ ሲሆን፤
5. የልማት ድርጅቱ የተከፈለው ካፒታል ውስጥ 75 በመቶ የሚሆነውን ሲያጣ፤ እና
6. የልማት ድርጅቱ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ መክሰሩ ሲታወጅ፡፡

42. <u>ስለመክሰርና ሂሣብ ማጣራት</u>

የልማት ድርጅቱን ኪሳራ እና ተያያዥ የንብረት ማጣራትን በተመለከተ የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

43.<u>ስለንብረት አጣሪዎች ሹመት፣ ተግባራትና ሥልጣን</u>

1. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ "የኢትዮጵያ ሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ያወጣው መስፈርቶች የሚያሟላ እና የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ያልሆኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ንብረት አጣሪዎችን ሊሾም ይችላል፤
2. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በበቂ ምክንያት ንብረት አጣሪዎችን በማሰናበት በአዲስ ንብረት አጣሪዎች ሊተካቸው ይችላል፤
3. ንብረት አጣሪዎች በመጣራት ላይ ያለውን የልማት ድርጅትን የሂሣብ ደብተርና ሰነዶች በይዞታቸው ሥር ያደርጋሉ፤
4. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፣ ንብረት አጣሪው የልማት ድርጅቱን በይዞታው ሥር ያደርጋል፤
5. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር፣ ንብረት አጣሪው የልማት ድርጅት ቦርድና የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፤

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረት አጣሪዎቹ በሂደት ላይ ያሉ ውሎችን ለማስፈጸም ወይም ለንብረት ማጣራቱ ጥቅሞች አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር አዲስ ሥራ መጀመር አይችልም፤
7. ቦርዱ የልማት ድርጅቱን የፋይናንስ አቋም በተመለከተ ለንብረት አጣሪዎች ሪፖርት ያዘጋጃል፤
8. ንብረት አጣሪዎችና ቦርዱ የልማት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በአጭሩ የያዘ የፋይናንስ አቋም መግለጫ በጋራ በማዘጋጀት ይፈርሙበታል፤
9. በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ንብረት አጣሪዎቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት እገዛ ያደርጉላቸዋል፡፡

44.<u>ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት</u>

1. ንብረት አጣሪዎች የልማት ድርጅቱ የሚፈርስ መሆኑን በማሳወቅ ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ በማስረጃ በማስደገፍ እንዲያቀርቡ ለገንዘብ ጠያቂዎች ያስታውቃሉ፤
2. ስማቸው በልማት ድርጅቱ መዝገብ ተመዝግቦ ለሚገኙ እና በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች የድርጅቱን መፍረስ በተመዘገበ ደብዳቤ እንዲያወቁ ይደረጋል፤ ሌሎች በድርጅቱ ያልተመዘገቡ ገንዘብ ጠያቂዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚሰራጭ ጋዜጣ በየሳምንቱ በሚወጡ ሶስት ተከታታይ ማስታወቂያዎች እንዲያውቁ ይደረጋል፤
3. ገንዘብ ጠያቂዎች ያሏቸውን የገንዘብ ጥያቄዎቻቸውን ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻው የጋዜጣ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዘጠና የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፤
4. ንብረት አጣሪዎች የልማት ድርጅቱን የፋይናንስ መግለጫ ከውሳኔ ሃሣቦች፣ ከገንዘብ ጠያቂዎች ዝርዝርና ክፍያ ከሚፈጽምበት ቅደም ተከተል ጋር በማዘጋጀት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፤
5. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የንብረት አጣሪዎች ያዘጋጁትን የሂሣብ መግለጫ መሠረት በማድረግና ያቀረቡትን ሃሣብ ከግምት ውስጥ በማስገባት፡-
   ሀ) የገንዘብ ጥያቄያቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያው እንዲፈጸም ይፈቅዳል፡፡

ለ) የልማት ድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ለገንዘብ ጠያቂዎች መክፈል ያለበት ዕዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሶስተኛ ወገኖችን መብት በማይነካ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በሚያጸድቀው የሽያጭ ዘዴ አማካይነት የልማት ድርጅቱን ንብረቶች ንብረት አጣሪዎች እንዲሸጡ ይፈቅዳል፡፡

45.<u>በገንዘብ ጠያቂዎች የሚደረግ ጥበቃ</u>

1. የታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ሊከፈላቸው የሚገባ ገንዘብ በገንዘብ ጠያቂዎቹ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ተቀማጭ ይሆናል፤
2. የልማት ድርጅቱን የሚመለከቱ ያልተጠናቀቁ ሥራዎችን ወይም ክርክሩ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ለገንዘብ ጠያቂዎቹ ዋስትና ያልተሰጠባቸው ክርክር ያስነሱ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ለብቻው ተለይቶ ይቀመጣል፤
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሠረት የልማት ድርጅቱ ህልውናውን ካጣ በኋላ በድርጅቱ መዝገቦች የማይታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ያላቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ገንዘባቸውን ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ከሰበሰበው ትርፍ ሀብት መጠየቅ ይችላሉ፡፡ በንብረት አጣሪዎች ቸልተኝነት የሚገባቸውን ክፍያ ያላገኙ ገንዘብ ጠያቂዎች ከንብረት አጣሪዎቹ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

46. <u>የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫ እና የመፍረስ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

1. ለገንዘብ ጠያቂዎች ክፍያ ከተፈጸመና በዚህ ደንብ አንቀጽ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ተቀማጭ ከሆነ በኋላ ንብረት አጣሪዎች የልማት ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ እና ለከተማ አስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ያሳውቃሉ፤
2. ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሚሰጠው አስተያየት ካለው ወዲያውኑ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ይልካል፤
3. በተቋጣጣሪ ባለሥልጣን ሥር ያለ የልማት ድርጅት የሚፈርስ ከሆነ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሀብትና ዕዳ መግለጫውን እንዳጸደቀ ወዲያውኑ የንብረት ማጣራቱ

ሥራ መጠናቀቁን ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ያስታውቃል፡፡ የአስተዳደሩ ካቢኔም የልማት ድርጅቱን ማቋቋሚያ ደንብ ይሽረዋል፤

4. የልማት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንቡ ከተሻረበት ቀን ጀምሮ ሕልውናውን ያጣል፤
5. የፈረሰው የልማት ድርጅት መዝገቦች በተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ዘንድ ለ10 ዓመት ይቀመጣል፡፡ በጉዳዩ ጥቅም ያለው ማንኛውም ሰው ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል መዝገቦቹን መመርመር ይችላል፡፡

47. <u>ተራፊ ሀብት</u>

ከፈረሰና ንብረቱ ከተጣራ የልማት ድርጅት የተረፈ ሀብት ለከተማ አስተዳደሩ ይተላለፋል፡፡

<u>ክፍል አስራ ሁለት</u>

<u>የአሰራር ሥርዓት</u>

48. <u>ስለዕቅድ ማጽደቅና የአፈፃፀም ግምገማ</u>

ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ፡-

1. በልማት ድርጅት የሚዘጋጁ የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች
   ሀ) ተገቢው የዕቅድ ይዘት ያለው፤
   ለ) የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል፣
   ሐ) ዕድገትና ትርፋማነት ሊያመጪ የሚችሉ፣
   መ) የመንግስት እና የህብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ፤
   መሆኑን በማረጋገጥ ያፀድቃል፤
2. የልማት ድርጅቶችን የዕቅድ አፈፃፀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያመች ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ አሰራር በመዘርጋት ይተገብራል፤
3. የልማት ድርጅቶች የዕቅድ አፈፃፀም በወቅቱ መከናወኑን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ የአፈፃፀም ጉድለት የታየባቸውን እንዲሻሻል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
4. የልማት ድርጅቶችን የስራ አፈጻጸም ጠቅላላ የሀብት መጠን፣ ዓመታዊ የገቢ መጠን፣ የተጣራ የትርፍ መጠን፣ የካፒታል መጠን፣ የልማት ድርጅቶቹን የሰው ሀይል እና ሌሎች አስፈላጊ መስፈርቶችን መሰረት አድርጎ ይመዝናል፣ ደረጃ ያወጣል ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ እውቅና ይሰጣል፣ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን ይደግፋል የተጠያቂነት ሥርዓት ያሰፍናል፡፡

49. <u>የኦዲት ሪፖርቶች ስለማጽደቅ</u>

1. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የልማት ድርጅቱ የሂሳብ እና ንብረት እንቅስቃሴ በየኦዲት ዓይነቱ የሙያ ብቃት ባላቸው፣ ነጻና ገለልተኛ በሆኑ፣ ሚስጥራዊ መረጃዎችን በጠበቀና ተገቢውን የኦዲት ቅደም ተከተል ጠብቆ የተሰራ መሆኑን በማረጋገጥ ሪፖርቱቱን ያጸድቃል፤

2. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የልማት ድርጅቶችን የኦዲት ግኝቶች መሠረት ተገቢው ማስተካከያና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

50. <u>ስለ አዳዲስ የፕሮጀክትና ኢንቨስትመንት አማራጮች</u>

1. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በአስተዳደሩ የገበያ ክፍተት የሚታይባቸውን የንግድ መስኮች በጥናት እንዲለይ ያደርጋል፤
2. በጥናት የተለየውን የገበያ ክፍተት ወደ ንግድና ኢንቨስትመንት አማራጭ በመቀየር የውሳኔ ሀሳቡን ለካቢኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ያስተገብራል፤
3. ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የልማት ድርጅቶች ገበያቸውን በማስፋት ትርፋማና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ተያያዥነት ያላቸውን የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ ያደርጋል፤ ለካቢኔ በማቅረብ ሲጸድቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
4. የልማት ድርጅቶችን ትርፋማና ውጤታማ የሚያደርጉ የኢንቨስትመንት ስራዎችን ለማከናወን የመንግስትና የግል አጋርነት ጋር በመቀናጀት ያከናውናል፤

51. <u>በልማት ድርጅቶች እና በአክሲዮን ማህበራት ውስጥ የመንግስትን የባለቤትነት መብት ስለማስከበር፤</u>

ባለስልጣኑ፡-

1. የልማት ድርጅቶችና የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ ላይ የመንግስትን ፍላጎትና የህብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ ይሰራል፣ ክትትል ያደርጋል፤
2. በአክሲዮን ማህበራት ውስጥ አስተዳደሩ ባለው የአክሲዮን ድርሻ መጠን የቦርድ አባላት እንዲመደቡ ለካቢኔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3. ከአክሲዮን የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ በወቅቱ መሰብሰቡን ይከታተላል፣ የትርፍ ድርሻውን በፈንድ አካውንቱ እንዲገባና ለሌሎች አዋጭ ኢንቨስትመንት እንዲውል ለካቢኔ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰን ያስፈጽማል፡፡

52.<u>የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም፤</u>

ባለስልጣኑ፡-

1. ከመንግስት የልማት ድርጅቶች መሰብሰብ ያለባቸውን ልዩ ልዩ መረጃዎች ይለያል፤ የመረጃ አሰባሰቡ ሥርዓት ተዘርግቶለት ወቅታዊ እና ጥራቱን የጠበቁ እንዲሆን የመረጃ ቋት እና የመረጃ ልውውጥ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ከአስተዳደሩ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በጋራ ይሰራል፤
2. ከልማት ድርጅቶች የሚያገኛቸውን መረጃዎች ያደራጃል፣ ይተነትናል ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ያደርጋል፤
3. ከልማት ድርጅቶች የሚያገኛቸውን ልዩ ልዩ መረጃዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችን በታቀደ መልኩ ያከናውናል፤
4. ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን የመረጃ አሰባሰቡን ዘመናዊ ለማድረግ የሚዘጋጁ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምና የመረጃ አያያዝ ደህንነት ላይ ለልማት ድርጅቶች ስልጠና የመስጠት እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

<u>ክፍል አሥራ ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

53.<u>ስለተሻረ ሕግ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ደንብ ቁጥር 14/1991 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

54.<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ የከተማው አስተዳደር ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

55.<u>የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

በዚህ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በአስተዳደሩ ባለቤትነት በተያዘ የልማት ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

56.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 53 የደንብ ቁጥር 14/1991 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንዲሁም ክፍል ሁለት ሁለት በሌላ ሕግ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፤
2. በደንብ ቁጥር 14/1991 መሰረት የወጣ መመሪያ ከዚህ ደንብ ጋር አስካልተቃረነ ድረስ በሌላ መመሪያ እስኪተካ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

57.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ከንቲባው ወይም ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

58.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከየካቲት 30 ቀን 2016 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 30 ቀን 2016 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ